በዓለም አቀፍ የቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ፌዴሬሽን

## የሕፃናትና ወጣት ጉልማሶች
## ቤተ-መፃሕፍት ክፍል

# የሕፃናት ቤተ-መፃሕፍት
# አገልግሎት የመምሪያ ሰነድ

## መነሻ

በዚህ በዛሬው ዓለም ውስጥ በኢኮኖሚያዊ፣ በባህላዊና በመገናኛ መስክ እየተካሄደ የሚገኘውን መጠነ ሰፊ ለውጥ እንዲቀበሉና እንዲደግፉ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብና የዚህ የመረጃ ዘመን ፍላጐቶች የቤተ መፀሕፍት ሙያንና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን እንደገና እየቀረጿቸው ይገኛሉ:: ይህ መምሪያ ሰነድ በሁሉም መጠን እና የኢኮኖሚ ደረጃዎች ለሚገኙ ቤተ መፃሕፍት እንደመጠቀሚያ መሣሪያ እንዲያገለግል ሆኖ ዋና ዋና መሪ ሃሳቦችን በሚያመለክት መልኩ በህፃናትና ወጣት ጐልማሶች ቤተ መፃሕፍት ክፍል ቋሚ ኮሚቴ አባላት የተዘጋጀ ነው::

ይህ መምሪያ ሰነድ በዓለም አቀፍ የቤተ መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ፌዴሬሽን እና በዩኔስኮ የተዘጋጀው የሕዝብ ቤተ መፃሕፍት ማኒፌስቶ፣ እንዲሁም የሕዝብ ቤተ መፃሕፍት አገልግሎት፣ የዓለም አቀፍ የቤተ መፃሕፍት ማህበራት ተቋማት ፌዴሬሽን እና የዩኔስኮ ለዕድገት መምሪያ፣ እና የቤተ መፃሕፍት አገልግሎት ለወጣት ጐልማሶች መምሪያ በሚሉ ርዕሶች የተዘጋጁት የፌዴሬሽኑ ሕትመቶች ደጋፊ አካል ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ነው::

## መግቢያ

የቤተ መፃሕፍት አገልግሎቶች በመላው ዓለም ለሚገኙ ህፃናትና ቤተሰቦቻቸው እንደዚህ እንደዛሬው ጊዜ መቼውንም ጊዜ ቢሆን አስፈላጊ ሆነው አያውቁም:: ወደዕውቀት እና በበርካታ ባህሎች ወደዳበረው የዓለም ብልጽግና የሚወስደው ጐዳና ክፍት እንዲሆንና እንዲመቻች ለማስቻል በህይወት ዘመን የማይቋረጥ ትምህርትና መሠረታዊ ትምህርት የማህበረሰባችን ቀዳሚ ትኩረት ሆነዋል:: በጥራት የተደራጁ የህፃናት ቤተ መፃሕፍት ህፃናት በህይወታቸው ዘመን የማይቋረጥ ትምህርትና መሠረታዊ የትምህርት ዕውቀት እንዲያገኙ በማስቻል በህብረተሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና የበኩላቸውን አስተዋጽዎ እንዲያበረክቱ ያስችሏቸዋል:: ቤተ መፃሕፍት በህብረተሰቡ ውስጥ እያደገ ለሚሄደው ለውጥ ምላሽ በመስጠት ህፃናት ያሏቸውን የመረጃ፣ የባህልና የመዝናኛ ፍላጐቶች ሊያሟሉላቸው ይገባል:: እያንዳንዱ ህፃን በአካባቢው የተደራጁ ቤተ መፃሕፍትን በአግባቡ የተላመዳቸውና ሳይጨነቅ የሚጠቀምባቸው መሆን ያለባቸው ሲሆን እንዲሁም በቤተ መፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙ ስብስቦችንና መጠቀሚያዎችን በቀላሉ ማግኘት የሚያስችለው ዕውቀት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል::

## ዓላማ

የዚህ መምሪያ ሰነድ ዓላማ በመላው ዓለም የሚገኙና በተለያዩ ሃገሮች ያሉት የህዝብ ቤተ መፃሕፍት ከፍተኛ ጥራት ያለው የህፃናት አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ መርዳት ነው::

## ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች

ይህ መምሪያ ሰነድ ትኩረት የሚያደርገው በቤተ መፃሕፍት ሥራ ላይ በተሰማሩ ባለሙያዎች፣ በቤተ መፃሕፍት የአስተዳደር ኃላፊዎችና ውሳኔ ሰጪዎች፣ እንዲሁም

በተማሪዎች እና በቤተ መፃሕፍትና የመረጃ ሳይንስ የሥልጠና ኘሮግራሞች መምህራን ላይ ነው፡፡

# ክፍል አንድ

## ተልዕኮ

የተለየዩ ማቴሪያሎችንና እንቅስቃሴዎችን በስፋት በማዘጋጀትና በማቅረብ የህዝብ ቤተ መፃሕፍት ለህፃናት ከንባብ የሚገኘውን ልዩ ደስታ እና እንዲሁም እውቀትንና የሰውን ልጅ የፈጠራ ውጤቶች በመረዳት የሚያገኙትን ልዩ የደስታ ስሜት እንዲያጣጥሙ ይረዳሉ፡፡ በተጨማሪም ህፃናትና ወላጆቻቸው በቤተ መፃሕፍቱ በጥሩ ሁኔታ እንዴት ሊጠቀሙ እንደሚችሉና በህትመትና በኤሌክትሮኒክ የመገናኛ መሣሪያዎች እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚችሉ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

የህዝብ ቤተ መፃሕፍት ለማንበብ የሚደረገውን የመማር ሂደት የመደገፍና መፃሕፍትንና ሌሎች የህፃናት የትምህርት መርጃ ዘዴዎችን የማስተዋወቅ ልዩ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ቤተ መፃሕፍቱ ለህፃናት የህፃናት ታሪኮችን የማንበብና ስለቤተ መፃሕፍቱ አገልግሎቶችና በቤተ መፃሕፍቱ ውስጥ ስለሚገኙ መጠቀሚያዎች የሚገልጹ ልዩ ዝግጅቶችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

በቀጣይ የህይወት ዘመናቸው የቤተ መፃሕፍት ተጠቃሚ ሆነው እንዲዘልቁ የሚረዳቸው ስለሆነ ህፃናት ከልጅነት ዕድሚያቸው ጀምሮ የቤተ መፃሐፍት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሊበረታቱ ይገባል፡፡

የተለያዩ ቋንቋዎች በሚነገሩባቸው ሃገሮች የሚገኙ መፃሕፍትና የኦዲዮ ቪዥዋል ማቴሪያሎች በህፃናት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች እንዲዘጋጁላቸው ያስፈልጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የህፃናትን ፍላጐቶች ስለማሟላት

የተባበሩት መንግሥታት የህፃናት መብት ድንጋጌ ህፃናት አቅማቸውን በተሟላ ብቁ ሁኔታ የማሳደግ እና እንዲሁም፣

- የዕድሜ
- የዘር
- የፆታ
- የሃይማኖት፣ የብሔራዊ ወይም የባህላዊ ማንነት
- የቋንቋ
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ደረጃ ወይም
- የግለሰባዊ ክህሎትና ችሎታ

ልዩነት ሳይደረግ ሁሉም በእኩልነት ነፃና ያልተገደበ መረጃ፣ ማቴርያልና ኘሮግራሞችን የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን አበክሮ ይገልፃል።

ህፃናት የሚያድጉት በሰፊው የዓለም እንቅስቃሴ ውስጥ ሳይሆን በቅርብ አካባቢያቸውና መንደራቸው ቢሆንም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታዩ አብይ ክንውኖች የራሳቸውን ተጽዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም።

## በቤተመፃሕፍቱ ሲገለገሉ የሚገባቸው

በግልም ሆነ በቡድን ሆነው ቢመጡ የሕፃናት ቤተ መፃሐፍት በራቸውን ክፍት አድርገው አገልግሎት ሊሰጧቸው ከሚገባው ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-

- በአነስተኛ እድሜ ላይ የሚገኙ ሕፃናት
- ቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚከታተሉ ሕፃናት
- ዕድሜያቸው እስከ 13 ዓመት የሆነ በትምህርት ላይ የሚገኙ ሕፃናት
- ልዩ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ወገኖች
- ወላጆችና ሌሎች የቤተሰብ አባላት
- ለህፃናት ጥበቃ ወይም እንክብካቤ የሚያደርጉ
- ከህፃናት ከመፃሐፍትና ከሚዲያ ጋር የሚሰሩ ሌሎች አዋቂዎች ናቸው።

## ግቦች

ህፃናት

- በመረጃ (ኢንፎርሜሽን)
- በሁሉም አይነት የመሰረታዊ ትምህርት
- በባህላዊ እድገት
- የንባብ ችሎታን በማበልጸግ
- በእድሜ ዘመን የማይቋረጥ ትምህርት እና
- በመዝናኛ ወቅት በሚደረጉ ልዩ ልዩ የፈጠራ ትርኢቶች ወይም ዝግጅቶች ዙሪያ ያላቸውን መብት መጠቀም እንዲችሉ መርዳት፣
- ህፃናት በሁሉም የቤተ መፃሐፍቱና መጠቀሚያዎችና የመገናኛ አገልግሎቶች (ሚዲያ) መጠቀም እንዲችሉ ያልተገደበ የመጠቀም ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ለህፃናት፣ለወላጆችና ለህፃናት ተንከባካቢዎች ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ማቅረብ፣
- የህፃናት ቤተሰቦች ወደ ቤተመፃሐፍቱ መግባት እንዲችሉ ተገቢውን ማመቻቸት፣
- ህፃናት በሁሉም ዘርፍ ያላቸው ብቃት የተሟላ እንዲሆን መርዳትና ስለ ነፃነታቸውና ስለ ደህንነታቸው ለሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ማሳወቅና ከጐናቸው መቆም፣
- ህፃናት በራሳቸው የሚተማመኑና ብቃት ያላቸው ዜጐች እንዲሆኑ መደገፍ፣
- ሰላም ለሰፈነባት ዓለም ተገቢውን ሁሉ ጥረት ማድረግ።

## የገቢ ምንጭ

የሚቻለውንና አቅም የፈቀደውን ሃብት በህፃናት ላይ እንዲውል ማድረግ ነገ በእርግጠኝነት መልካም የተሻለ ምርት በሚሰበሰብበት ጉዳይ ላይ እንደዋለ ሐብት የሚቆጠር ነው።

የሚሰጡት አገልግሎትና የቤተ መፃሐፍቱም አጠቃላይ አቅርቦት ጥራት ያለው እንዲሆንና እንዲሻሻል ለማድረግ የህፃናት ቤተ መፃሐፍት በጀት ሊመደብላቸው ይገባል።

መደበኛው በጀት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሌሎች የውጭ የዕርዳታ የገቢ ምንጮች ሊደገፍ ይገባዋል፡-

- ከመንግሥት የሚገኝ የበጀት ድጐማ (በተለይም ለልዩ የፕሮግራም ዝግጅትና አዳዲስ የፈጠራ ክንውኖች)
- ከባህላዊ ዝግጅቶች (ከሙዚቃ፣ ዳንስ፣ ድራማ፣ ስነ-ጥበብ፣ እንዲሁም ከታሪካዊና ብሔረሰባዊ ዝግጅቶች)
- ከአሳታሚዎች (ፀሐፊዎችና መፃሐፍት ላይ የሚገኙ ስዕሎችን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ለሚያደርጓቸው ጉብኝቶች ወይም ሌሎች ስጦታዎች)
- ከስፖንሰሮች (በአካባቢው የሚገኙ የንግድ ድርጅቶችና የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ለልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የሚያደርጉት ድጋፍ)
- መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች
- እና ሌሎች ተመሳሳይ አግባብነት ካላቸው የገቢ ምንጮች

## ማቴሪያሎች

የሕፃናት ቤተ መፃሕፍት ለህፃናት አጠቃላይ እድገት አግባብነት አላቸው የሚባሉና በተለያየ መልክ የሚገኙ በህትመት መልክ የተዘጋጁ መጠቀሚያዎች (መፃሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ኮሚኮች እና በራሪ ጽሑፎች)፣ ሚዲያዎች (ሲዲዎች፣ ዲቪዲዎችና ካሴቶች)፣ አሻንጉሊቶች፣ እያጫወቱ የሚያስተምሩ መጫወቻዎች፣ ኮምፒውተሮች፣ ሶፍትዌሮችና የኢንተርኔትና ሌሎች የመገናኛ መጠቀሚያዎችንና የመሳሰሉትን አደራጅተው ሊይዙ ይገባል።

## የምርጫ መመዘኛዎች

የሕፃናት ቤተ መፃሕፍት ባለሙያዎች የመጠቀሚያ ስብስቦችንና አገልግሎቶችን በሚያደራጁበት ወቅት መጠቀሚያዎቹ

- ከፍተኛ ጥራት ያላቸው
- የተጠቃሚዎቹን ዕድሜ የሚመጥኑ
- ወቅታዊ እና በሁሉም መመዘኛዎች ትክክል የሆኑ
- የተለያዩ እሴቶችንና አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ
- የአካባቢውን ህብረተሰብ ባህል የሚያንፀባርቁ
- ዓለም አቀፋዊውን ህብረተሰብ የሚያስተዋውቁ መሆናቸውን ሊያረጋግጡ ይገባል።

**የመጠቀሚያ ምናሬዎች**

በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት ሁልጊዜም ቤተ መፃሕፍቱን ለአገልግሎት ዝግጁ፣ የሚስቡና የሚማርኩ፣ ለዕውቀትና ለዕድገት የሚደክሙበትና ህፃናቱ ለመሄድ የማይፈሩበት ሥፍራ ሆኖ ሊያገኙበት ይገባል።

በሕዝብ ቤተ መፃሕፍት ውስጥ የሚገኝ የሕፃናት አገልግሎት በተቻለ መጠን በቀላሉ ሊለይ የሚችል (ለምሳሌ ልዩ መገልገያዎች፣ ጌጦችና ቀለማት ያሉት) የራሱ የማንበቢያ ክልል ያለውና ከሌላው የቤተ መፃሕፍት ክፍል ተለይቶ ሊገኝ የሚገባው ነው። ቤተ መፃሕፍት ህፃናት እርስ በርሳቸው ወይም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አማካይነት ሌሎች በርቀት የሚገኙ ህፃናትን ሊገናኙ የሚችሉበትን መድረክ የሚያበጅ ሥፍራ ነው።

**አገልግሎቶች**

የሕፃናት አገልግሎቶች በጣም አስፈላጊ ተደርገው ሊወሰዱና ከአዋቂዎች አገልግሎት በእኩልነት ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው።

የሕፃናት ቤተ መፃሕፍት

- የተለያዩ መጠቀሚያዎችን በማዋስ፣
- የመረጃና አስፈላጊ መረጃዎችን በፍጥነት ለማግኘት የሚያስችሉ የማጣቀሻ አገልግሎቶችን በመስጠት፣
- ሕፃናት የሚፈልጓቸውን መጠቀሚያዎች መምረጥ እንዲችሉ በመርዳት፣
- ሕፃናቱ ቤተ መፃሕፍቱ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚችሉ መጠቀሚያዎችን በመምረጥና በቤተ መፃሕፍቱ አገልግሎት አደረጃጀት ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ፣
- በቤተ መፃሕፍት አጠቃቀምና በተሟላ የመረጃ ዕውቀት ላይ ሥልጠና በማዘጋጀት፣
- ሕፃናት እንዲነቃቁ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን በማደራጀት (ለምሳሌ ንባብን ማበረታታት የመሳሰሉ)
- አዳዲስ ኘሮግራሞችንና የሕፃናት መፃሕፍት ትረካዎችን በማቅረብ፣
- ወላጆችንና ሕፃናትን የሚንከባከቡ ወገኖችን በማስተማር፣
- ሕፃናትን ለሚንከባከቡ፣ ለቅድመ መደበኛና ለመደበኛ ትምህርት መምህራንና ለቤተ መፃሕፍት ባለሙያዎች አስፈላጊ መረጃዎችን በፍጥነት ለማግኘት የሚያስችሉ የማጣቀሻ አገልግሎትና ሥልጠና በመስጠት፣
- ከማህበረሰባዊ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር በመተባበርና በተቻለ መጠን እነሱንም በመደገፍ፣

የማህበረሰቡን ሕፃናት የመረጃ፣ የባሕላዊና የመዝናኛ ፍላጐቶች ሊያሟሉላቸው ይገባል።

**ስለትብብር**

በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ሌሎች ድርጅቶችና ተቋማት ጋር የትብብር ቅንጅት መፍጠር አስፈላጊና ጠቃሚም ነው።

- የአካባቢው ማህበረሰብ የመረጃና የባህል ፍላጐቶች ምን እንደሆነ ማጥናትና እነዚህ ፍላጐቶች በቤተ-መፃሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙ መጠቀሚያዎች ጋር እንዲጣጣሙ ለማድረግ በመጣር በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ ተቋማት እርስ በርሳቸው የሚፎካከሩ ሳይሆን ለሕፃናት ጥቅም የሚተባበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
- ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ የትብብር አካሎች ናቸው። በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ቤተ-መፃሕፍት ለትምህርታዊ ሂደቱ ድጋፍ የሚሰጡ ሲሆን የህፃናት ቤተ-መፃሕፍት ደግሞ ለግላዊ ትምህርትና ለመዝናኛ የሚሆኑ ንባቦችን የሚያዘጋጁ ናቸው።
- በህፃናት፣ በወላጆችና በፕሮፌሽናሎች ዘንድ የንባብን ጥቅም ከማስረጽ አንፃር የጤና ጣቢያዎች፣ የህፃናት የቀን ማቆያ ሥፍራዎች፣ መዋዕለ ህፃናትና ሌሎች የእንክብካቤ ሥፍራዎች አስፈላጊና ሊታለፉ የማይችሉ የትብብር ተቋሞች ናቸው።

## ስለማስተዋወቅ

የሕፃናትን ጊዜና አትኩሮት ለማግኘት ፉክክሩ እየተጠናከረ በሚሄድበት ወቅት የህፃናት ቤተ-መፃሕፍት ገንቢና ሕዝባዊ ዕይታ እንዲያገኙ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ንባብ እና መሠረታዊ ትምህርት ለመግባቢያ አስፈላጊ ክህሎቶች ሲሆኑ ይህ እሴታቸው ሁልጊዜም ከፍ ተደርጐ ሊታይ ይገባዋል።

## ስለሰው ኃይል

ውጤታማና በዘመናዊ አደረጃጀት የሚመሩ የህፃናት ቤተ-መፃሕፍት የሰለጠኑና ጽኑ የሥራ ፍላጐት ያላቸው የህፃናት ቤተ-መፃሕፍት ባለሙያዎች ያስፈልጓቸዋል።
ስለዚህም ከባለሙያዎቹ የሚጠበቀው ክህሎት፡-

- ከፍ ያለ የመሥራት ፍላጐት
- ግንኙነት የመፍጠር፣ ከሰዎች ጋር የመግባባት፣ በቡድን የመሥራትና መፍትሔ የመስጠት ከፍተኛ ችሎታ
- ቅንጅት የመመስረትና ተባብሮ የመሥራት ችሎታ
- አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የአካሄድ መስመር የመቀያየርና ለለውጥ ዝግጁ መሆን
- የተጠቃሚዎችን ፍላጐት የመመዘን፣ የማቀድ፣ አገልግሎቶችንና ዝግጅቶችን የመምራትና የመገምገም
- አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር መትጋትና ሙያንም በየጊዜው ማዳበር

በተጨማሪም የሕፃናት ቤተ መፃሕፍት ባለሙያዎች

- በህፃናት ሳይኮሎጂና ዕድገት
- ንባብን በማዳበርና ስርፀት ንድፈ ሃሳብ
- በሥነ ጥበባዊና በባህላዊ ዝግጅቶች አቅርቦት እና

- በመፃሕፍትና በሌሎች ተመሳሳይ ሚዲያዎች ውስጥ በሚገኙ የሕፃናት ሥነ ጽሑፎች ላይ በቂ ዕውቀትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

## ስለአመራር እና ምዘና

በአጠቃላይ የቤተ-መፃሕፍት እቅድና ግብ ውስጥ ለህፃናት ቤተ-መፃሕፍት የተለየ ግንዘቤና ድጋፍ እንዲኖር ማድረግ ይቻል ዘንድ ለህፃናት አገልግሎት አመራር የሚሰጡ ሁሉ በቤተ መፃሕፍቱ ሁለገብ የዕቅድ ሂደት ውስጥ መሳተፋቸው አስፈላጊ ነው።

ቤተ-መፃሕፍቱ ተግባራቸውን በአግባቡ እየተወጡ ስለመሆናቸው ለማወቅ የሚረዳ አስተማማኝ መረጃ መያዝ ቤተ-መፃሐፍቱን በቅጡ ለመገምገምና ለማሻሻል የሚያግዝ አስፈላጊ መሣሪያ ነው።

- ለዕቅድ የሚረዳ መረጃ ለማግኘት፣ ተጠያቂነትን ለማሳየትና በመረጃ የተደገፈ የአመራርና ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል በሃብት፣ በሰው ሃይል፣ በአገልግሎት፣ በማዋስ ሥራና በመሳሰሉት ላይ እስታቲስቲክስ መሰብሰብና መያዝ ይገባል።
- ደረጃውን በጠበቀ የሥራ ብቃት ላይ በመመርኮዝ በአገልግሎቱ ላይ የተሰማሩ ሠራተኞችን የሥራ አፈፃፀም መለካት ወይም መመዘን ያስፈልጋል።

## ክፍል ሦስት

### የእርስዎ አስተዋጽዖ ይፈለጋል

- የሕፃናትና ወጣት ጉልማሶች ቤተ-መፃሕፍት ክፍል ቋሚ ኮሚቴ የእርስዎን አስተዋጽዖ ይፈልጋል።
- በዓለም አቀፍ የቤተ መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ፌዴሬሽን የመረጃ መረብ (ዌብ ሳይት) ላይ እንድናካትተው ለማድረግ እባክዎን የመልካም የሥራ ምሳሌ መልዕክት ካለዎት እንዲልኩልንና የክፍላችን አባል እንዲሆኑ እንጠይቃለን።
- የሚልኩልን መረጃ ወይም አስተያየት ካለዎት እባክዎን በኮሚቴው ሊቀመንበር ወይም የመረጃ አስተባባሪ በኩል ይላኩልን።

## ለተጨማሪ መረጃዎች

ይህ ሰነድ በዓለም አቀፍ የቤተ-መፃሕፍት ማህበራትና ተቋማት ፌዴሬሽን የሕፃናትና ወጣት ጉልማሶች ቤተ-መፃሕፍት ክፍል የተዘጋጀና በክሮሺያ አገር ዛግሬብ ከተማ ከሚገኘው የሜድቬቻክ የሕዝብ ቤተ-መፃሕፍት ጋር በጥምር የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት ነው (ዲሴምበር 2003)

በክፍሉ እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ፍላጐት ካደረብዎ የፌዴሬሽኑ አባል በመሆን በክፍላችን ሊመዘገቡ ይችላሉ።

ለተጨማሪ መረጃና ለዝርዝር ጉዳዮች በፌዴሬሽኑ የመረጃ መረብ (ዌብ ሳይት) አድራሻ www.ifla.org ላይ የሚገኘውን የክፍላችንን የመረጃ ቦታ ይመልከቱ።

የዚህን መምሪያ ሰነድ የህትመት ቅጂ ማግኘት ከፈለጉ በመረጃ አስተባባሪው በኩል ለማዘዝ ይችላሉ።

ይህ መምሪያ ሰነድ የተመሰረተው በክፍሉ በተቋቋመ የጥናት ቡድንና ተባባሪዎቹ በተዘጋጀው ረቂት መነሻ ጽሑፍ ላይ ነው። www.ifla.org/vll/s10/scl.htm ይመልከቱ።